*መልእክት አምስት*

## ድል ነሺ ለመሆን የክርስቲያንን ሕይወት የመኖር ምሥጢር—
## እንደ የሕይወት ዛፍ ክርስቶስን የመመገብና የመደሰትን መንገድ መከተል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 2፥9፤ ራእ 2፥7፤ ዮሐ. 6፥57፣ 63፤ ኤር. 15፥16፤ መዝ. 119፥15፤ ሕዝ. 3፥1-4

**I. ድል ነሺ እንሆን ዘንድ የክርስቲያንን ሕይወት የመኖር ምሥጢር ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመብላትና የመደሰትን መንገድ መከተል ነው፤ እግዚአብሔር ምንም ነገር እንድናደርግለት አልወጠነም፤ የእርሱ ብቸኛ ፍላጎት ለድሰታችን ራሱን እንደ መብል ለእኛ መስጠት ነው፤ ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመደሰትን መንገድ የሚከተሉ ብቻ ሕይወታቸውንና ሥራቸውን በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ውስጥ ዘልቆ ያዩታል—ዘፍ. 2፥9፤ ራእ. 2፥7።**

**II. በጸሎት ሁሉና ቃሎቹን በማሰላሰል እና መንፈስና ሕይወት የሆኑትን ቃሎቹን በመብላት ሕይወት-እንደየሚሰጠው መንፈስ ጌታ ኢየሱስን በመቀበል ለድሰታችን እርሱን እንደ መንፈሳዊ መብላችን ልንመገበው እንችላለን—ዮሐ. 6፥57፣ 63፤ ኤር. 15፥16 እና የግርጌ ማስታወሻው፤ ኤፌ. 6፥17-18፤ መዝ. 119፥15 እና የግርጌ ማስታወሻው፤ ማቴ. 4፥4፤ መዝ. 119፥103፦**

ሀ. መንፈስና ሕይወት የሆኑትን ቃሎቹን በመብላት ጌታ ኢየሱስን ስንመገብ፣ *ከ* እርሱ *የተነሣ* እንኖራለን (ዮሐ. 6፥57፣ 63)፤ የምንኖረው *በ* ክርስቶስ ሳይሆን እንደ የሚያጠነክረን ንጥረ-ነገራችንና የአቅርቦታችን ምክንያት *ከ* ክርስቶስ *የተነሣ* ነው፤ ክርስቶስን በትንሣኤው እንኖራለን፣ ክርስቶስን በመመገብ እንኖራለን (ገላ. 2፥20፤ ፊልጵ. 1፥19-21)።

ለ. ቃሉን በመብላት ጌታ ኢየሱስን ስንመገበው፣ ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ ማብላላት ሊኖረን ያስፈልገናል—ሕዝ. 3፥1-4፤ ኤር. 15፥16፤ ራእ. 10፥9-10፦

1. ጥሩ ማብላላት ካለን፣ ምግቡ ወደ የውስጠኛው ማንነታችን እያንዳንዱ ክፍል እንዲገባ ክፍት ማለፊያ መንገድ ይኖረዋል፤ በመመገብ ማብላላት አለን፣ በማብላላት ማዋሐድ አለን እና በማዋሐድ የክርስቶስን ብልጥግናዎች ተግባራዊ ምግብ ወደ ማንነታችን ውስጥ እናስገባለን—ኤፌ. 3፥8፣ 16-17።
2. የምግብ አለመብላላት ማለት ጌታ እንደ መንፈሳዊ ምግብ ወደ የውስጥ ክፍሎቻችን የሚገባበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም ማለት ነው፤ ምግቡ ወደ ውስጥ ክፍሎቻችን የሚገባበት ነፃ መንገድ ሳይኖረው ሲቀር የምግብ አለመብላላት ይኖረናል—ዕብ. 3፥12፣ 15፤ 4፥2።
3. መንፈሳዊ ምግብ በውስጣችን ክፍት ማለፊያ መንገድ ይኖረው ዘንድ መላው ማንነታችንን ከሁሉም የውስጥ ክፍሎቻችን ጋር ለጌታ ክፍት አድርገን መጠበቅ አለብን፤ ይህን ካደረግን ተገቢ የሆነ የምግብ ማብላላትና ማዋሐድ ይኖረናል፣ ክርስቶስን እንደ መንፈሳዊ መብል ወደ ውስጣችን እንቀበላለን፣ ለእግዚአብሔር መገለጥም ክርስቶስ ቅንብራችን ይሆናል—ኤፌ. 3፥16-17፤ ቆላ. 3፥4፣ 10-11።

**III. የተራቡትንና የተጠሙትን ለማርካት የአብን ፈቃድ በማድረግ እና በሂደት ላለፈው ሦስታንዱ አምላክ ክብር የአምላክ-ሰው ሕይወትን በመኖር በምድር ላይ አብን በማክበር ክርስቶስን ልንመገበው እንችላለን—ማቴ. 24፥45-47፤ ፊልጵ. 1፥19-21፦**

ሀ. "እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ...የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው"—ዮሐ. 4፥32፣ 34።

ለ. "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ" (ዮሐ. 17፥4)፤ እግዚአብሔርን ማክበር በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን መግለጥ ነው (ተዛ. ቆላ. 1፥9-11)።

ሐ. በስብዕና ኑሮው ጌታ የአብን ፈቃድ ሁልጊዜ እንዲመርጥ ኃይል የሰጠውን ቅቤ (እጅግ የበለጠገውን ጸጋ) እና ማር (ጣፋጩን ፍቅር) ተመገበ—ኢሳ. 7፥14-15፣ "አሜሪካን ስታንዳርድ ቨርዥን" የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም።

መ. እኛ "እውነት በኢየሱስ እንዳለ" ክርስቶስን የምንማር ነን፤ *እውነት በኢየሱስ እንዳለ* የሚለው በአራቱ ወንጌላት እንደተዘገበው የጌታ ኢየሱስን እውነተኛ የሕይወት ሁኔታ፣ ለአማኞቹ ምሳሌ ለመተው በምድር ላይ አብን ያከበረበትን ሕይወት ያመለክታል—ኤፌ. 4፥20-21፦

1. ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለማክበር ሁሉን በእግዚአብሔር ውስጥ፣ በእግዚአብሔር እና ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገበትን ሕይወት ኖረ፤ እግዚአብሔር በኑሮው ውስጥ ነበር፣ ከእግዚአብሔር ጋርም አንድ ነበር፤ ሕይወታችን ለመሆን ወደ እኛ ውስጥ መግባት ይችል ዘንድ በትንሣኤ ሕይወትን-የሚሰጥ መንፈስ ሆነ፤ በተፈጥሮአዊ

ሕይወታችን ሳይሆን በትንሣኤ እንዳለ ሕይወታችን (ቆላ. 3፡4፤1ጴጥ. 2፡21) በእርሱ ምሳሌ መሠረት ከእርሱ እንማራለን (ማቴ. 11፡29)።

2. ጌታ ኢየሱስ አንድም ነገር ከራሱ አላደረገም (ዮሐ. 5፡19)፤ የራሱን ሥራ አልሠራም (4፡34፤ 17፡4)፣ የራሱን ቃል አልተናገረም (14፡10፣ 24)፣ የራሱንም ፈቃድ አላደረገም (5፡30)፣ የራሱንም ክብር አልፈለገም (7፡18)።
3. ክርስቶስን መማር ማለት የክርስቶስን ምሳሌ ቅርጽ መያዝ፣ ማለትም፣ የክርስቶስን መልክ መምሰል ነው፤ እርሱ ራሱ በውስጣችን እንደሚያድረው መንፈስ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ፣ ከሕይወቱ ብልጥግናዎች ሁሉ ጋር በእኛ ውስጥ ራሱን ያባዛል—ሮሜ 8፡2፣ 28-29።

ሠ. ኢሳይያስ 43፡7፣ "በስሜ የተጠራውን፣ ለክብሬም የፈጠርሁትን፣ የሠራሁትንና ያደረግሁትን ሁሉ" ይላል፤ ለእግዚአብሔር ልንሰጠው የምንችለው ከፍተኛው አገልግሎት ክብሩን መግለጥ ነው—2 ቆሮ. 3፡18፤ ሮሜ 9፡23።

ረ. አንደኛ ቆሮንቶስ 6፡20 "በዋጋ ተገዝታችኋልና። ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" ይላል፤ ይህ በውስጣችን የሚኖረው እግዚአብሔር (1 ዮሐ. 4፡13)፣ አካላችንን እንዲሞላው እና እንዲያጥለቀልቀው እና እንደ የእርሱ መቅደስ ራሱን በአካላችን እንዲገልጥ መፍቀድ ነው (1 ቆሮ.6፡19)፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡31፣ "የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት" ይላል።

## IV. ተገቢ ከሆኑ ሰዎች ጋር በመገናኘት እርሱን መመገብ እንችላለን—ዘሌ. 11፡1-3፣ 9፣ 13፣ 21፡-

ሀ. መብላት ከእኛ ውጭ ያሉ ነገሮችን መንካት እና ወደ ውስጣችን መቀበል ነው፣ ውጤቱም በሂደት ውስጣዊ ቅንብራችን መሆናቸው ነው፤ በዘሌዋውያን 11 ሁሉም እንስሳት የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ያመለክታሉ፣ መብላትም ከሰዎች ጋር መገናኘታችንን ያመለክታል (የሐዋ. 10፡9-14፣ 27-29)፤ በቅዱሱ እግዚአብሔር ጥያቄ መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅዱስ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ፣ ስለሚያገኟቸው ሰዎች ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው (ዘሌ. 11፡46-47፤ 1 ቆሮ. 15፡33፤ 2 ቆሮ. 6፡14-18፤ 2 ጢሞ. 2፡22)።

ለ. ሰኮናቸው የተሰነጠቀ እና የሚያመሰኩ እንስሳት (ዘሌ. 11፡3፣ ቁ.4-8፣ 26-28) በእንቅስቃሴያቸው ውስጥ መለየት (ማስተዋል) ያላቸውን (ፊልጵ. 1፡9-10) እና የእግዚአብሔርን ቃል በብዙ ጥንቃቄ በተሞላበት ማሰላሰል የሚቀበሉ ሰዎችን (መዝ. 119፡15) ያመለክታሉ።

ሐ. ክንፍና ቅርፊት ያላቸው የውኃ ውስጥ እንስሳት በዓለም ውስጥ በነፃነት መንቀሳቀስ እና መሥራት፣ በተመሳሳይ ጊዜም ተጽእኖውን መቋቋም የሚችሉ ሰዎችን ያመለክታሉ (ክንፎች ዓሦችን በውኃ ውስጥ እንደየፍላጎታቸው ለመንቀሳቀስ፣ ለመሥራት ያግዛቸዋል፣ ቅርፊቶች በባሕር ውስጥ የሚኖሩትን እነዚህን ዓሦች ጨዋማ ከመሆን የሚከላከሉ እና የሚጠብቁ ናቸው)—ዘሌ. 11፡9።

መ ለመብረር ክንፍ ያላቸው እና እንደ የምግብ አቅርቦታቸው የሕይወትን ዘሮች የሚበሉ ወፎች፣ ከዓለም ውጪ እና በላይ በሆነ ሕይወት ውስጥ መኖር እና መንቀሳቀስ የሚችሉትን እና የሕይወትን ነገሮች እንደ የሕይወት አቅርቦታቸው የሚወስዱ ሰዎችን ያመለክታሉ—ቁ. 13።

ሠ. ክንፍ ያላቸው እና ከእግሮቻቸው በላይ በምድር ላይ ለመዝለል እግሮች ያሏቸው ነፍሳት ከዓለም በላይ በሆነ ሕይወት መኖር እና መንቀሳቀስ የሚችሉትን እና ራሳቸውን ከዓለም መጠበቅ የሚችሉ ሰዎችን ያመለክታሉ—ቁ. 21-22።

## V. በአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ በስብሰባዎች በእርሱ ላይ በዓል በማድረግ እርሱን መመገብ እንችላለን፡-

ሀ. የእስራኤል ልጆች የመልካሚቱን ምድር ፍሬ በሁለት መንገዶች ሊደሰቱ ይችላሉ፣ የተለመደው፣ የግል መንገድ በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ቦታ እና ከማንም ጋር እንደ የጋራ ድርሻ መደሰት ነበር (ዘዳ. 12፡15)፤ ልዩው፣ የጋራው መንገድ ከእስራኤላውያን ሁሉ ጋር በተወሰኑት በዓሎች እና በእግዚአብሔር በተመረጠው ልዩና ብቸኛ ስፍራ ከፍተኛውን ድርሻ፣ በኩራቱን መደሰት ነበር (ቁ. 5-7፣ 17-18)።

ለ. በተመሳሳይ ሁኔታ የአዲስ ኪዳን አማኞች የክርስቶስ ድሰታ ሁለት ገጽታዎች ያሉት ነው፡- በማንኛውም ጊዜ እና በማንኛውም ቦታ ክርስቶስን የመደሰት የተለመደ፣ ግላዊ ገጽታ እና በስብሰባዎች ላይ ልዩና ብቸኛ በሆነው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ ተገቢ በሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ስብሰባዎች ውስጥ፣ በእግዚአብሔር በተመረጠው ስፍራ ላይ የክርስቶስን ከፍተኛውን ድርሻ የመደሰት ልዩው፣ የጋራ ገጽታ ነው።

## VI. እግዚአብሔር ለሰው የወጠነው ውጥን፣ ሰው ይደሰተው ዘንድ እንደ የሕይወት ዛፍ ራሱን ለሰው መስጠት ነበር፤ እግዚአብሔር እንድንደሰተው መፈለጉን እና ለእርሱ ምንም እንድናደርግለት አለመፈለጉን ማየት የክርስትና ሕይወት ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመደሰት ጉዳይ መሆኑን ማየት ነው፤ እነዚህን ሁለት ነጥቦች እናይ ዘንድ ጽንሰ-ሃሳባችን ከተለወጠ፣ እግዚአብሔርን የመደሰት ሕይወትን መኖር ቀላል ይሆንልናል።

© 2022 Living Stream Ministry